## የባእዳን እጆችን ከኦሮምያ ላይ ለማስነሳት ዘርፈ-ብዙ ትግል ማፋፋም

## የወቅቱ ኣብይ ጥያቄ ነው

የወያኔ መንግስት ባለፉት 21 ኣመታት ኣምባገነናዊ ኣገዛዙ ኦሮሞና መሰል ተጨቋዋኝ ህዝቦችን ሲያደማ መኖሩ ግልጽ ነው። የኣምባገነናዊ ኣገዛዙ ረቂቅ ስልቶችን ከመቀመር ኣንስቶ ስራ ላይ እስከማዋል ድረስ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው የስርኣቱ ቁንጮ ደግሞ መለስ ዜናዊ ነበር። የዚህ ሰይጣናዊ ቡድን የጭካኔ እርምጃዎች በተነሱ ቁጥር የመለስ ዜናዊ ስም ኣብሮ ሳይጠቀስ ያለፈበት ወቅት ኣልነበረም። ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ የሰብኣዊ መብት ተሟጋቾችና የስርኣቱ ኣገዛዝ የሚያሳስባቸው የውጭ መንግስታት መለስን እያነሱት መተቸትና ማውገዝ የተለመደ ጉዳይ ነው።

መለስ ዜናዊ ዛሬ ሞቷል። ካሁን ወዲያም ተመልሶ ኣይመጣም። በህዝቦች ላይ የፈፀመው በደል ከልክ ኣልፎ ሞልቶ በመፍሰሱ ሳይሆን ኣይቀርም፣ የተፈጥሮ ፍርድ ኣግኝቶ ሲያቆስላቸውና ሲያደማቸው ከኖረው ህዝቦች ጫንቃ ላይ ወርዶ ዳግም ላይመለስ ሄዷል። የጭካኔ ኣገዛዙን ኣውርሶት የሄደው ስርኣት ግን በቦታው ነው። በሃጢያታዊ የኣገዛዝ ስልት ዘላለም የህዝብ ደም እንደጠጣ መኖር የሚፈልገው ስርኣቱ በመሪው ድንገተኛ ሞት ተደናግጦ ቆም ብሎ ራሱን የሚገመግምበት እድል ተፈጥሯል። በዚህ ውድ እድል ተጠቅሞ ራሱን ለመገምገም ግን ስርኣቱ ኣሁን የፈቀደ ኣይመስልም። ፈጣሪው መለስ ዜናዊ ኣውርሶት የሄደውን የኣምባገነናዊ ኣገዛዝ ስትራቴጂና ስልቶችን እንዳለ ለመቀጠል እየፎከረ ይገኛል። ይህ ደግሞ የመለስ ዜናዊ ሙት መንፈስ ኣርፎ እንዳይተኛ ከማድረግ በቀር የስርኣቱን እድሜ ለማራዘም ኣቅም ኣይኖረውም። ወያኔዎች የታላቁ መሪያቸው ኤከራ ኣርፎ እንዲተኛ ከፈለጉ መለስ በኣገዛዝ ዘመኑ የፈፀማቸውን ጥፋቶች የማረም ድፍረት ማግኘት ይጠበቅባቸዋል።

ኣሁን የመለስን ሞት ተከትሎ ምን ይመጣ ይሆን የሚለው የብዙዎች ጥያቄ ነው። እንደ ኦሮሞ ያሉት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሁል ጊዜ ተገዢ የሆኑ ህዝቦች የጨቋዋኙን መሪ ሞት ተከትሎ ነጻነት በኣቋራጭ ይገኝ ይሆናል የሚል ተስፋ ሊታያቸው ይችላል። መታወቅ ያለበት ሃቅ ግን ተጨቋዋኞቹ ህዝቦች እንዲህ ባለው እድል ተጠቅመው የነፃነት ብርሃን ለማግኘት የሚመኙትን ያህል ጨቋዋኞች ደግሞ እድሉን ተጠቅመው ዳግም የጭቆና ኣገዛዛቸውን ሊያጠናክሩበት ከመትጋት እንደማይቆጠቡ ነው። የመለስን ሞት ተከትሎ በግልጽም ሆነ በስውር የሚስተዋለው እውነታም ይሄው ነው።

ባሁኑ ጊዜ ሶስት ኣይነት የፖለቲካ ፍልሚያዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ። የመጀመሪያው በራሱ በህወሃት ኣመራር ውስጥ የመለስን ወንበር ለመያዝ የሚደረገው የስልጣን ሽኩቻ ነው። ሁለተኛው ኣይነት ፍልሚያ ቀደም ሲል ወደተነጠቁት ስልጣን ለመመለስ በሚፍጨረጨሩና በህወሃት መካከል የሚካሄደው ነው። ሶሶተኛው ደግሞ እንደ ኦሮሞ

ያሉ የተገፉና የተጨቆኑ ህዝቦች ሁለቱንም ሃይሎች ባለመፍቀድ የሚያደርጉት ፍትሃዊ የመብት ትግል ነው።

በህወሃት ውስጥ እየተካሄደ የሚገኘው የስልጣን ሽኩቻ መዘዝ የሚያስከትለው ቀውስ ፈንድቶ የሚወጣበት ጊዜ ሩቅ አይመስልም። ይህንን የህወሃቶች የስልጣን ሽኩቻ በቅርበት የሚከታተሉት ብአዴኖች በበኩላቸው የእድሉን አመቺነት ራሳቸው ሊጠቀሙበት ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላሉ። ህወሃቶችና ብአዴኖች በዚህ አይነቱ ውሳኝ ወቅት የበፊቱ አጋራችን የሚሉት ኦፒዲኦ እንዲቀርባቸው አይፈቅዱም። ኦፒዲኦ ብዙሃኑን የኦሮሞ ህዝብ እወክላለሁ ሲል ከተጠቀሱት ሁለቱ ሃይሎች በላቀ መልኩ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ስልጣን እንዲሰጠው የሚያስችል መብት ቢኖረውም ይህንን መብቱን ለማስከበር አባላቱ በገሃድ ሲከራከሩ ተሰምቶ ኣያውቅም። ኦፒዲኦ በኦሮሞነት ግርማ ሞገሱ ቆሞ ይህንን የመብት ጥያቄውን እንዳያስመልስ ተብሎ ማእከላዊ ኮሚቴውና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አፋን ኦሮሞ መናገር በሚችሉትና በብሄር ግን ኦሮሞ ባልሆኑት ግለሰቦች ተሞልቶ በቁጥጥር ስር ወድቆኣል። ህወሃቶችና ብአዴኖች የየራሳቸውን ድርጅቶች እንደያዙ ኦፒዲኦን ደግሞ በተጨማሪነት በሞግዚት አስተዳዳሪዎቻቸው አማካኝነት መቆጣጠር ወስነዋል። ከኦፒዲኦ አመራሮች መሃል ብዙዎቹ የሚገባቸውን የጠቅላይ ሚኒስትርነት መብት አውቀው መከራከር ይቅርና ባሁኑ ወቅት በወያኔ ህወሃት ጉዋዳ ምን እየተከናወነ እንደሚገኝ እንኩዋን የሚያውቁት አይመስሉም። ኦፒዲኦ የሚፈለገው እርስ በስር ከሚቀናቀኑት የሰሜን ባላንጣ ሃይሎች መካከል አንዱ አሸንፎ በመውጣት የመሪነቱን ቦታ ሲጨብጥ በተላላኪነት ለማገልገል እንዲታዘዝ ብቻ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ህገ መንግስቱ በሚደነግገው መሰረት የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ለመተካት መብትና ግዴታ የተሰጠው ለተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤው ለአባዱላ ገመዳ ወይም ለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ቢሆም የነዚህ ሰዎች እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ግልፅ አይደለም። በትውልዱም ሆነ በህይወት ታሪኩ ከህወሃቶች ጋር ምንም አይነት ትስስር የሌለው ሃይለማሪያም ደሳለኝ በአብዛኞቹ የህወሃት አንጋፋ ታጋዮች ዘንድ ጉሮሮ ውስጥ የተወተፈ አጥንት ተደርጎ እየታየ ነው። ሃይለማሪያምን ከሩቅ ጎትቶ ከዚህ ቦታ በማስቀመጡም ወያኔዎቹ ምናልባት የመለስን ሙት መንፈስ እየረገሙ ሳይሆን እንደማይቀር መገመት ይቻላል።

ትላንት ወደ ተነጠቁት ስልጣን ለመመለስ የሚያልሙ ሃይሎች ወያኔን የሚኮንኑት በብሄር ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ስርኣት ዘርግቶ የሃገሪቷን አንድነት ኣላላ በማለት ነው። ከዚሁ ጋር ኣያይዞም የህዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የሚፈቅድ አንቀጽ በህገ መንግስቱ ውስጥ ኣካተተ በማለት ኣምርረው ይወቅሱታል። እንደ ኦሮሞ ያሉት የሃገር ባለቤትነት መብታቸውን የተነፈጉ ህዝቦች ደግሞ ወያኔ ለራሱ ጥቅም ሲል በወረቀት ላይ ባፀደቀው ህገ መንግስት መሰረት ጥያቄያቸው ኣጥጋቢ ምላሽ ስላላገኘ በህገ መንግስቱ ላይ በተለይም በኣንቀፅ 39 ስር የተቀመጠው መብት ሙሉ በሙሉ

ገቢራዊ እንዲሆን ይታገላሉ። ወያኔ ህወሃት በፖለቲካ ኣላማቸው የምስራቅና የምእራብ ያህል ልዩነት ባላቸው ሁለቱ ሃይሎች መካከል ባለው ቦታ ሰፈረ።

የስርኣቱ ቁንጮ የነበረው መለስ ዜናዊ እንደ ኦሮሞ ያሉ የተገፉ ህዝቦች በኣንድ ወገን የሚያነሱትን ጥያቄና የቀድሞው ስርኣት ናፋቂዎች በሌላው ወገን ያነገቡትን ጥያቄ ወደ ጎን በማለት በራሱ የኣመራር ስትራቴጂ ሁለቱንም ሃይሎች ከስልጣን በማራቅ ዘላለም እንደመራ መኖር የሚችለው ኢህኣዴግ ብቻ ነው ብሎ ራሱን ኣሳመነ። እንደ ኣስታራቂ ሃይል ራሱን ሰይሞ ህዝቦችንና ኣለም ኣቀፉ ማህበረሰብን ለማታለል የሚያመቸውን የብልጣብልጥነት ፖሊሲ ነድፎ ስራ ላይ ኣዋለ። ኢህኣዴግ በስልጣን የሌለ እንደሆነ ሃገሪቷ ሁለት ቀን እንኳዋን ማደር ኣትችልም፥ ህዝቦቹ ኣንደ ኣውሬ ሊባሉ ይችላሉ እያለ ሽብር ፈጥሮ በመንዛት ኢትዮጵያን ከመፈራረስ ማዳንና የምእራባዉያኑን ጥቅም ማስከበር የሚችለው እሱ ብቻ እንደሆነ በማስመሰል ኣሳየ። በዚህም "በሳልና ኣርቆ ኣስተዋይ የሃገር መሪ" የሚል ስም ሸመተበት። ተጨቁዋኝ ህዝቦች በኣንድ በኩል የሚያነሱትና የቀድሞ ስርኣት ኣላሚዎች በሌላ በኩል የሚያነሱት ጥያቄ በቀላሉ የሚታረቅ ሆኖ መገኘቱ ወያኔ ለ21 ኣመታት ስልጣን ላይ እንዲኖርና ነገም በዚሁ መልኩ በስልጣን ለመቀጠል እንዲመኝ ኣደፋፈረው።

በዚህ ጥገናዊ ለውጥ ኢምፓየሪቷን ጠግኖ ለዘላለም ማስቀጠል እንደማይቻል ግን መለስ ዜናዊ ይረዳ ነበር። የሃገሪቷን የኣንድነት መሰረት በቀላሉ በማይናድ ኣሸዋ ላይ ኣንጸናል እያለ በምላሱ ይናገር እንጂ ኢትዮጵያ ይበልጥ በኣደጋ እንደተከበበች መሆኗን ውስጡ ኣላጣውም ነበር። ስለዚህም በኣሻጥር የተሞላ ፖሊሲውን ወደ ተግባር በመለወጡ ሂደት ውስጥ ኣንዲት ትንሽ ስህተት ኣደጋ ማስከተል እንደምትችል ስለሚገነዘብ በሁሉም የኣስተዳደር ቦታዎቹ ላይ ለይስሙላ ያህል የስራ ሃላፊዎችን ይሰይም እንጂ በራሱ ቀጥተኛ ኣስተዳደራዊ መዋቅር እጁን እያስገባ ማስፈፀምና መቆጣጠርን መረጠ። ስለሆነም ላለፉት 21 ኣመታት ኢህኣዴግን በስልጣን ላይ ያቆየው የኣንድ ግለሰብ ሁለገብ ሚና ነው ማለት ይቻላል።

ከላይ የተነሱትን እውነታዎች የመገምገሙ ኣስፈላጊነት ወደፊትስ ከኛ ምን ይጠበቃል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያግዛል። የኦሮሞ ህዝብ ምን እንደሚፈልግ ግልፅ ነው። የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በይፋ ተግባራዊ ሆኖ በሃገሩ ኦሮምያ ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት ማረጋገጥ ይፈልጋል። ከማናቸውም የሌላ ብሄር ተፅእኖ ተላቅቆ በሃገሩ ላይ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የቁዋንቁዋና የባህል መብቶችን በኣስተማማኝ ሁኔታ ጨብጦ በሙሉ ስልጣን ራሱን በራሱ ማስተዳደር ይሻል። በርግጥ ትላንትናና ዛሬ በህዝባችን ዘንድ የተለያዩ ትርጉሞች እንዳሏቸው ኣሙን ነው። እኛ እናውቅልሃለን የሚሉትን ሃይሎች ኣሳፍሮ ለመመለስ የሚያስችል ኣስተማማኝ ንቃተ ህሊና ኣዳብሯል። የሚሆንለትን ራሱ ያውቃል። ፍላጎቱን ለመወሰን የሚያስችል ጠመንጃ መታጠቅ ብቻ እንደቀረውም ይረዳል። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት ልጆቹ ዛሬ የተሻለ የትምህርት እድል ስላገኙ በህዝባቸው ታላቅነትና ሃገራቸው ኦሮምያ በታደለችው ጸጋ ይኮራሉ እንጂ ሌሎችን መስለው ለማደር ራሳቸውን ኣያሞኙም። ይህ

የማይካድ ሃቅ ሲሆን በትላንትናና በዛሬ መካከል ያለው ትልቁ ልዩነትም ነው። በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ከተመዘገቡት ድሎች መካከል ኣንዱም ይሄው ነው።

ይህ ድል ካሁን ወዲያ ማንኛውም ሃይል በኦሮሞ ጫንቃ ላይ ለመቆናጠጥ ኣንዳያልም ትልቅ የማስጠንቀቂያ መሳሪያ ሆኖ ማገልገል ይገባዋል። በሚፈጠሩት ማናቸውም ሁኔታዎች ውስጥ የኦሮምያን የኣስተዳደር መዋቅሮች ይበልጥ ማጠናከርና ሌሎች ሃይሎች የኦሮምያን ሉኣላዊነት ለመዳፈር እጃቸውን የሚሰዱባቸውን ቀዳዳዎች ሁሉ ደፍኖ ተስፋ ማስቆረጥ የግድ ይሆናል። ኦሮሞነቱ የሚሰማው የኦሮሞ ተወላጅ ሁሉ በቁጭት ተነሳስቶ መታገል ለነገ የሚባል ኣይደለም። ኦሮሞ በሃገሩ ላይ የሚገባውን የባለቤትነት መብት ገቢራዊ እንዳያደርግ ሳንካ ሊሆንበት የሚፈልገውን ሃይል ሁሉ ለመቀልበስ መንቀሳቀስ የወቅቱ ኣንገብጋቢ ጥያቄ ነው።

ኦፒዲኦ ውስጥ የተሰለፉ የኦሮሞ ልጆችም ቁጭት ኣድሮባቸው ላለፈው ጥፋታቸው ይቀርታ በመጠየቅ በሙሉ ልቦና ከህዝባቸው ትግል ጎን የሚሰለፉበት እጅግ ወሳኝ ጊዜ ኣሁን ነው። ኦሮሞነት የሚሰማው ማንኛውም ዜጋ በፈለገው ኣይነት የፖለቲካ መዋቅር ውስጥ ቢገኝም እንደ ኦሮሞነቱ ካለበት በመቀናጀትና በመሰባሰብ ኦሮምያን የማዳን እርምጃ በጋራ የመውሰድ ሃላፊነት ተጥሎበታል። በኦሮምያ ጫንቃ ላይ ለመፈራረቅ የሚያስካኩ ባእዳን ሃይሎች ከኦሮምያ ላይ እጃቸውን እንዲያነሱ የማሳሳብና ጥረታቸውንም የማጨናገፉን ትግል ማፋፋም የወቅቱ ኣብይ ጥያቄ ነው!

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ